

# የሞባይል ጥገና

በEthio-ቴክ

ሞባይል ሁለት ክፍሎች አሉት።

1. **ሃርድዌር (Hardware) ፡-** *በእጃችን የምንነካው ወይንም የምንዳሰው በሙሉ **hardware** ይባላል።*

2. **ሶፍትዌር(Software) :-** *የሃርድዌር ክፍል እንዲሰራ የሚያደርገው እና በእጃችን መንካት የማንችለው ግን ሲሰራ የምናየው ክፍል ሶፍትዌር (**Software**) ይባላል።*

# የሞባይል ሃርድዌር ጥገና መሳሪያዎች ና አጠቃቀማቸው

# ሀ. ዲሲ ፓወር ሰፕላይ (DC Power Supply)

ይህ መሳሪያ ዋና ስራው

- *ስልካችን በባትሪ አልነሳም በሚልበት ወቅት የባትሪውን ቦታ በመተካት ስልካችን ማስነሳት፤*
- *ስልካችን አልነሳም ያለ ከሆነ ይህን መሳሪያ በመጠቀም ምክንያቱን ማወቅ (ችግሩ ከሃርድዌር ወይስ ከሶፍትዌር ነው የሚለውን ለመለየት)*
- *የሞተ ባትሪ ለመቀስቀስ (እንደገና እንዲሰራ)*




Fig :- **DC Power Supply**

# ለ. ሆት ኤር ገን / ሆት ኤር ብለወር (Hot Air Gun / Hot Air Blower)

- *ይህ መሰረያ ሙቀት እና ንፋስን በመጠቀም የተለያዩ የሞባይል ክፍሎችን የምንጠግንበት ነው።*
- *ይህ መሰረያ በተለይ ሞባይላችን ላይ ያሉ የተለያዩ አይሲዎች ለማሞቅ፣ ለማንሳት ና ለመቀየር ይረዳናል።*




Fig :- ***Hot Air Gun /SMD Work Station/***

# ሐ. መልቲሜትር (Multimeter)

- *ይህ መሰረያ በሞባይላችን ላይ ያሉ የተለያዩ ዕቃዎችን (ለምሳሌ ማይክ፣ ስፒከር፣ ቫይብሬተር...) መስራት ና አለመስራታቸውን ለማረጋገጥ እንጠቀምበታለን።*
- *ይህ መሰረያ በዋነኛነት continuity እና voltage ለመመልከት ይረዳናል።*



Fig :- **Multimeter**

# መ. ቫይብሬተር (Vibrator/PCB Cleaner tool)

- *ይህ መሰሪያ ሻርት ያደረጉ፣ የዛጉ ወይም የቆሸሹ የሞባይል ቦርዶችን በቲነር በመዘፍዘፍ ለማፅዳት ይረዳናል።*




Fig :- **PCB cleaner tools**

# ሠ. ቴኒቲን (Thinner)

- *የሞባይል ቦርድላይ ያሉ ዝገቶችን፣ ሾርቶችን እና ቆሻሻዎችን በብሩሽ በመጠቀም ለማፅዳት እንጠቀምበታለን።*
- *ብዙ ጊዜ ግን isopropyl የተባለ አልኮል ነው የምንጠቀመው sanitizerም መጠቀም ይቻላል።*




Fig :- ***Thinner (isopropyl alcohol)***

# ረ. ካውያ (Soldering iron)

- *ይህ መሳሪያ ሞባይላችን ላይ ያሉ ተበያጅ ክፍሎችን ሊድ በመጠቀም በመበየድ ለማያያዝ እንጠቀምበታለን።*



Fig :- **Soldering Iron**

# ሰ. ሊድ (Lead)

- *ሊድ ሞባይላችን ላይ መበየድ የሚገባቸው ክፍሎችን ካውያን በመጠቀም ስንበይድ ለማያያዝ የሚረዳን ነው።*


RS PRO
Lead Free
FluxCore
Sn100E
0.040' Dia
1.02mm
NCFlux
3.3% Flux
Lot#
P/N 0.25Kg
RS800-7664

Fig :- **Lead**

# ሸ. ጃንፐር ሽቦ (Jumper Wire)

- *የጃንፐር ሽቦ ሞባይላችን ላይ ያሉ የኤሌክትሪክ መንገዶች ሲቋረጡ ለመቀጠል ይረዳናል*
- *ይህ ሽቦ በፕላስቲክ የተሸፈነ ስለሆነ መስመሮችን ለመቀጠል በምንፈልግበት ጊዜ ጫፎችን መላጥ ያስፈልጋል።*



Fig :- **Jumper Wire**

# ቀ. ፔስት (Paste flux)

- *ሞባይላችን ላይ ያሉ የተለያዩ ክፍሎችን በብሉወር ወይም ካውያ በመጠቀም በምንጠግንበት ወቅት ቦርዱ በሙቀት እንዳይጎዳ የምንጠቀመው ቅባት ነው።*




Fig :- ***Paste Flux***

# በ. መፍቻዎች (Screw Driver)

- *በጥገና ወቅት ሞባይላችንን ለመፍታትና ለማሰር የምንጠቀመው ነው።*



Fig :- **Screwdriver Set**

# ተ. ቦርድ ማሰሪያ (PCB Holder)

- *ይህ መሳሪያ በተለይ በብሎወርን በመጠቀም አይሲዎችን እና ለሎች የሞባይል ክፍሎችን ስናነሳ ቦርዳችን እንዳይነቅቃነቅ አስረን የምንይዝበት ነው።*




Fig :- **PCB Holder**

# ቸ. ቲዊዘር (Tweezer)

- *ይህ መሳሪያ በሞባይል ጥገና ወቅት አይሲዎችን እና ሌሎችንም ዕቃዎችን ከሞባይል ቦርድ ላይ ለማንሳት፣ ለማስቀመጥና ደግፎ ለመያዝ እንደ 3ተኛ እጅ እንጠቀምበታለን።*




Fig :- **Tweezer**

ይቀጥላል.....